# አቶ ገዱ በብዙ ኢትዮጵያዉያን ዘንድ የለዉጡ አካል ናቸዉ

ሚክይ ዓምሃራ

አቶ ገዱ አሁን ላይ ናሽናል ፊገር ሁነዋል፡፡ በብዙ ኢትዮጵያዉያን ዘንድ የለዉጡ አካል ናቸዉ በማለት ይሞገሳሉ፡፡ አቶ ገዱ ምናልባትም ወደ መጨረሻዉ የፖለቲካ ዘመኑ እየደረሰ ይመስለኛል፡፡ ቀጣይ የሚሆነዉ ጡረታ መዉጣት ነዉ፡፡ በዚህ ወር ዉስጥ ብአዴን እራሱን እንደገና እንደሚያዋቅር ባለፈዉ አስታዉቋል፡፡ እንዴት እንደሚያዋቅር ባላዉቅም ለአቶ ገዱ ግን ይሄን ልምከራቸዉ፡፡ አቶ ገዱ የክልል ፕሬዝደንትነታቸዉን በዚህ ወር ዉስጥ ቢጨርሱ በሚከተሉት ምክንያቶች የተሻለ ነዉ እላለዉ፡፡

1. አቶ ገዱ ወደ ፌደራል ቢሄዱ እና በሚኒስትርነት ቢያገለግሉ እንደኛበአገር አቀፍ ደረጃ ባላቸዉ ተቀባይነት የክልል መሪ ሁኖ የፖለቲካ ህይወትም መጨረስ ለእራሰቸዉ ፕሮፋይልም ጥሩ አይደለም፡፡ ስለዚህም አሁን ያላቸዉን እዉቅና በመጠቀም የሀገሪቱ የአንዱ ሚኒቴር ሁነዉ ቢሰሩ ፕረሰናሊ ለራሳቸዉ ታሪክ ነዉ፡፡ ከክልል ወይም አዉራጃ መሪዎች ይልቅ በታሪክም በሰፋት የሚታወሱት የሀገር ሚኒስቴር ሁነዉ የሰሩ ሰወች ናቸዉ፡፡ ስለዚህም የሚቀጥሉትን ሁለት አመታት ወደ ፌደራል ሄደዉ ቢሰሩ የተሻለ ነዉ፡፡

2. አቶ ገዱ አሁን ላይ በተሻለ ሁኔታ የፌዴራሉን ፖለቲካ በቅርበት ያዩት ይመስለኛል፡፡ ከህወሃት ጋርም ከኦህዴድ ጋርም በባለፉት 1 አመት በተካሄደዉ የዉስጥ ሽኩቻ ዋና ተካፋይ በመሆናቸዉ ፌደራል ላይ ቢሄዱ የአማራን ህዝብ ብሎም የኢትዮጵያን ህዝብ በተሻለ ያገለግላል፡፡

3. አቶ ገዱ በሌሎች ክልሎች ዘንድም ከፍተኛ ተቀባይነት አትርፈዋል ለምሳሌ በኦሮሚያ ስለዚህም ፌዴራል ላይ በመሆን በሌሎች ክልሎች የሚኖሩ አማሮችን ጥቅም ለማስጠበቅ ያለዉን ተቀባይነት በመጠቀም መስራት ይችላል፡፡ የመፈናቀልና መሰል ችግሮች ቢፈጠሩም ጉዳዩን በተሻለ ሁኔታ ለመፍታት ይሰራል ብየ እገምታለዉ፡፡

ዶ/ር አምባቸዉን የክልል መሪ ማድረግ

አቶ ገዱን ወደፌድራል በመዉሰድ ዶ/ር አምባቸዉን ወደ ክልል መመለስ የተሻለ ነዉ ባይ ነኝ፡፡ ዶ/ር አምባቸዉ ፌዴራል አካባቢ ተጽእኖዉ ያን ያህል ነዉ፡፡ ክልሉ ላይ ግን በወጣቶች ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ የመጣ ሰዉ ነዉ፡፡ የዶ/ር አምባቸዉ የክልሉ መሪ መሆን አንድ ሁለት ጥቅሞች ይኖሩታል፡፡

1. ዶ/ር አምባቸዉ በትምህርቱም እስከ ፒ.ኤ.ች ዲ የደረሱ መሆኑ ለብዙ የአማራ ወጣቶችና ሙሁራኖች ሮል ሞዴል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ብዙ የተማሩ ወጣቶች ወደ ፖለቲካዉ እንዲቀላቀሉ እንደ አነሳሽ ሊሆን ይችላል፡፡ በብዛት በዱካዉ ለሚፈርመዉ የድርጅቱ አባልም ማሸማቀቂያ ይሆናል፡፡

2. ዶ/ር አምባቸዉ ለወጣት እና ለተማረ ሰዉ ቀና አመለካከት አለዉ ስለዚህም የሚቀጥሉት ሁለት አመታት ወጣቶች እና ሙሁራን በሚፈልጉት መንገድ እንዲደራጁ እና እንዲንቀሳቀሱ ጥሩ እድል ይፈጥራል ባይ ነኝ፡፡ ዶክተሩም ወጣቶችን ብዙ ጊዜ ተደራጁ የአማራን ህዝብ ችግር እኛ ብቻ አንፈታዉም ሲል በተደጋጋሚ ስብሰባወች ላይ ሲገልጽ ይታያል፡፡ ባጠቃላይ እንደዚህ ቢያደርጉ ትቂት የተሻለ ሊሆን ይችላል፡፡ይመስለኛል

መላኩ ፋንታም ባለፈዉ ከሪፖርተር ጋር ያደረገዉን ሰፊ ቆይታ በጥሞና አነበብኩት፡፡ ሰዉየዉ የሀገሪቱን ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ በሚገባ የተረዳ ሰዉ ሁኖ አግኝቸዋለዉ፡፡ እሱም የሆነ ቦታ ቢሰጠዉ የተሻለ ያገለግላል ብየ አምናለዉ፡፡

የብአዴን የሰሞኑ ስብሰባ ሰዉን በሰዉ መተካት ብቻ እንዳልሆነ እና ሌሎች ብዙ ጉዳዮችን እንዴት ሊያያቸዉ እንደሚችል የሚከተሉትን ጉዳዮች ላንሳ፡፡

ምድብ አንድ፡ የአማራ ህዝብ ጥያቄወች

---

የአማራ ህዝብ በተለያዩ ሰልፎች ያነሳቸዉ የህገመንገስት ጉዳይ፤ የማንነት የእነ ወልቃይት ጉዳይ ከሱዳን ጋር ስላለዉ ደንበር፤ ከክልሉ ዉጭ ስላሉት አማራወች የፖለቲካ ዉክልና፤ በቋንቋቸዉ የመማር የመዳኘት እና ባህላቸዉን የማሳደግ መብት (ይህ ሁሉ ህገመንግስቱ ላይ ሊነሳ ይችላል)፡፡ የአማራ ህዝብ የፍትህ፤ የኢኮኖሚ እና የእኩል ተጠቃሚነት ሁኔታ፡፡ የክልሉ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀዉስ (የመንገድ፤ የትምህርት ቤት፤ የስራ አጥነት፤ የጤና፤ የኢንደስትሪ እና የመሳሰሉት)፡፡ በሸወች የሚቆጠሩ ታስረዉ በማንነታቸዉ ታስረዉ የተፈቱ እንዲሁም ለአካለ ጎዶሎነት የተዳረጉ፤ አሁን መኖሪያ ቤት እንኳን የሌላቸዉ እንዴት ይቋቋሙ ፍትህስ እንዴት ያገኛሉ፡፡ ድርጅቱ ለነሱ ምን አስቧል፡፡ ቀሪ የፖለቲካ እስረኞች በተለይም በክልሉ እና በፌደራል እስር ቤቶች ስላሉት፡፡ የክልሉን የፍትህ ስርአት እንዴት ሪፎረም ሊያደርግ አስቧል፡፡

ሁሉንም ጸረ አማራ ጸረ ለዉጥ እና ጸረ አገር ከድርጅቱ ልቅም ብሎ መዉጣት አለበት፡፡የክልሉ ህገመንግስት እና የኮሙኒስት ባንዴራዉ ጉዳይ አብሮ እዚሁ ዉስጥ መካተት ይችላል፡፡

ምድብ ሁለት፡ ብአዴን እና ድርጅታዊ አላማዉ/ቁመናዉ ወይም እረዮተ አለሙ ምንድን ነዉ

---

ከዚህ በመቀጠል ብአዴን እራሱን ሊጠይቅበት የሚችላቸዉን አይቸዉ ሰንደቅ የሚባል ጓደኛየ የላከልኝን ጥያቄ ትቂት በማሻሻል አቀርበዋለዉ፡፡
ድርጅታዊ ቁመናዉ፣ የአባላት አመላመሉና አያያዙ፣ አባላቱ ምን ያህል ድርጅታቸዉን እነደሚያዉቁ፣ የድርጅቱ መገለጫወች ምንነትና ወካይነት፣ ከነማን ጋር ስትራቴጃዊ አጋርነት እንዳለዉና የአጋርነቱ አላማ፣ ለምን እንደተቋቋመ፣ የተቋቋመበት ዓላማ፣ ርዕዮት አለሙ፣ ስትራቴጅዉ፣ የትኛዉን ህዝብ እነደሚወክል፣ የሚወክለዉ ህዝብ የት እነደሚገኝ፣ የሚወክለዉ ህዝብ አገሩ የት እንደሆነ፣ እወክለዋለዉ ከሚለዉ ህዝብ ምን እነደሚፈልግ፣ እስካሁን ድረስ እወክለዋለሁ ለሚለዉ ህዝብ ያስገኘዉ ጥቅም፣ እወክለዋለዉ የሚለዉን ህዝብ ስነልቦና የማወቅ አቅሙ፣ ወከልኩት የሚለዉን ህዝብ የታሪክ ዳራ የመረዳት አቅሙ፣ የነገሮችን መለወወጥ የመረዳትና በፍጥነት የመወሰን አቅሙ፣ የኢትዮጵያን የምስራቅ አፍሪካንና የአለምን የፖለቲካና የፀጥታ ኃይሎች አሰላለፍ የመረዳት አቅሙ አይገባኝም፡፡

እንዲሁም የኢትዮጵያን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ፣ የኢትዮጵያን ህገ መንግስትና ሌሎች አገራዊና ክልላዊ ህጎች ምንነትና ያላቸዉን ተፅዕኖ የማወቅ አቅሙ፣ የሚወክለዉ ህዝብ የትና በምን መለኩ የአገር ባለቤትና ልዋላዊ የስልጣን ባለቤት እነደሆነ፣ የኢትዮጵን ፌደራሊዝም ተጨባጭ ምንነትና አረዳዱ፣ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ያለዉ የተጨበጠ የስልጣን ተሳትፎ፡፡ ብአዴን ምን አይነት ሀገር እንድትመሰረት ነዉ እያሰበ ያለዉ እንደ ድርጅት ድርሻዉ ምንድን ነዉ፡፡ የአማራ ህዝብ አሻራ እየተካሄደ ባለዉ የአገር ግንባታ በምን መልኩ ነዉ የሚንጸባረቀዉ፡፡

ምድብ ሶስት፡ ስለብሄራዊ ጭቆና

---

ኢትዮጵያ ዉስጥ ብሔራዊ ጭቆና ነበር? ብሔራዊ ጭቆና ምን ማለት ነዉ? ብሔራዊ ጭቆና ማን በማን ላይ ነዉ ያደረሰዉ? ጨቋኙ ማን ነዉ? ተጨቋኙስ ማን ነዉ? መቸ ነዉ ጭቆናዉ የነበረዉ? ጭቆናዉ የቆመዉ መቸ ነዉ? ጭቆናዉን ማን አቆመዉ? ጭቆናዉን ለማቆም የጨቋኙና የተጨቋኙ፣ እንዲሁም የሌሎች አካላት ድርሻ ምን ነበር? በጭቆና ዉስጥ ጨቋኙ በመጨቆኑ ምን አገኘ፣ ምን አጣ? በጭቆና ዉስጥ ተጨቋኙስ በመጨቆኑ ምን አጣ፣ምን አገኘ? ጭቆናዉ ቁሞ ከሆነ ለጨቋኙና ለተጨቋኙ ምን

ዉጤት አስገኘ? ጭቆናዉ ለምን ቆመ? የጭቆና መገለጫወች ምንድን ናቸዉ? በጨቋኝ ተጨቋኝ ትርከት ዉስጥ ማነ ተስማማ፣ ማን አልተስማማም? ለምን? ጨቋኙና ተጨቋኙ በጭቆና ወቅት የት ነበሩ? ዛሬስ አሉ? ካሉ የት ነዉ ያሉት?

ምድብ አራት ስለአማራ ገዥ መደብ እና የአማራ ማንነት

——-

አማራንና አማርኛን በማገናኘት የአማራ ገዥ መደብ የሚል ትርክት ብዙ ተብሎለታል፡፡ ከጥያቄ ምድብ ሶስት ጋራ በማያያዝ የአማራ ገዥ መደብ በሚለዉ ላይ በአሁኑ ጊዜ የብአዴን አቋም ምን ይመስላል?
ወላጆቻችን ኢትዮጵያን በደም እና ባጥንታቸዉ ገንብተዉ አቆይተዉልናል፡፡ እኔ አማራ ነኝ፡፡ ያደኩት በቅኔ፣ በዜማ፣ በሽለላ፣ በቀረርቶ፣ በፉከራ፣ በዘይቤ፣ በታሪክ፣ በተረትና ምሳሌ፣ በፈሊጣዊ አነጋገር፣ በዘፈን፣ በእስክስታ ነዉ፡፡ እነዲሁም በደስታዉ፣ በሰርጉ፣ በሐዘኑ፣ በእድሩ፣ በእርቅ፣ በሽምግልና፣ በሐይማኖት; በማህበር፣ በአገር ወረራ አደጋ የማንነቴ መገለጫዎችን የሚጠቀም ማህበረሰብ ዉስጥ ነዉ፡፡
እነዚህ ቅርሶችና እሴቶች የማንነታችን መገለጫወች ናቸዉ፡፡ አባቶቸና እናቶቸ አገራቸዉን ከጠላት የጠበቁበት፣ የፍልስፍናቸዉ፣ የስነ ልቦናቸዉ፣ የስነ አዕምሯቸዉ፣ የሐይማኖት፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብራቸዉ፤ የፖለቲካ፣ የድፕሎማሲ፣ የስነ ጥብብ፣ የከዋከብት፣ የስነ ምድር፣ የስነ ፍጥረት፣ የመሰተጋብር፣ የአመራር፣ የባህል ትዉፊቶቻቸዉና የስልጣኔያቸዉ መገለጫቸዉ ናቸዉ፡፡ያደኩበት ማህበረሰብ ብዙ የታሪክ ባለቤት ነዉ፡፡ በዚህም አማራዉ አገር በመገንባት ከሌሎች እህትና ወንድሞቹ ኢትዮጵያዊያን ብሄሮች ጋር በመሆን የተከበረቸና የታፈረች የነጻነት ተምሳሌ የሆነች አገር አቆይቷል፤ አስረክቧል፡፡ ይህም በአለም ላይ ተመስክሮለታል፡፡ ለዚህም ብዙ የፊደል፣ የቋንቋ፣ የጽሁፍ፣ የሰነድ፣ የባህል፣ የእርሻ፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣ የስነ መንግስት፣ የስነ ጥብብ፣ የታሪክና የስነ ህነጻ ማስረጃወች አሉ፡፡ የአማርኛ ቋንቋንም አሳድጎና አበልጽጎ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ለእድገትና ብልጽግና አገራዊ በሆነ ኩራት ይጠቀምበት ዘንድ አስርክቧል፡፡በአሁኑ ጊዜ እነዚህን የማንነቴ፣ የአማራ፣ የኢትዮጵያ ዋልታና ማገር ዕሴቶችን በስፋት ብጠቀም፣ ባሳድግ፣ ባበለጽግ፣ ለትዉልድ ባስተላልፈፍ ትምክተኛ፣ ጠባብ፣ ጎጠኛ፣ አክራሪ፣ ጽንፈኛ፣ ነዉጠኛ፣ አሸባሪ፣ ተላላኪ፣ ጠላት፣ ዘረኛ፤ ጨቋኝ፣ ነፍጠኛና የድሮ ስርአት ናፋቂ የሚለል ታርጋ ይለጠፋል?

በዚህ ላይ ብአዴን እንደ አማራ ድርጅት ምን አስተያየትና አቋም አለዉ? የአማራ ህዝብ ይሄን ያህል ስቃይ በማንነቱ ሲደርስበት እንዴት ዝም አለ፡፡ በማንነቱ ከስራ ሲባረር እንዴት ዝም አለ፡፡ 40 ሺህ ወታደሮች በማንነታቸዉ ሲቀነሱ እንዴት ዝም አለ፡፡ ሰወችን ከመቀያየሩ ጎን ለጎን አኒህ እና መሰል ጥያቄወች ላይ ብአዴን ያለዉን አቋም አጀንዳ አድርጎ ተወያይቶ ማሳወቅ አለበት፡፡ እንግዲህ ቅርበት ያላችሁ ሰወች አድርሷቸዉ፡፡

ለዛሬዉ እና ለሰሞኑ ያለኝ ነገር ይሄዉ ነዉ፡፡
ሚከይ ዓምሃራ